## መመሪያ ቁጥር 107/2014
## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የወጣት ስብዕና መገንቢያ ማእከላት የአስተዳደርና አገልግሎት አሰጣጥ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር የሚገኙ ወጣቶች ከተለያዩ ማሕበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግሮች ተላቀው በከተማውና በአገራዊ ልማት ንቁ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማስቻል የወጣቶች ስብዕና መገንቢያ ማዕከላት ጉልህ አስተዋፅኦ እንዳላቸው በመታመኑ፤

የወጣቶች ስብዕና መገንቢያ ማዕከላት በተጠናከረ፣ ቀጣይነት ባለውና ወጣቶችን ባሳተፈ መልኩ ወጣቶች በአካል፣ በአዕምሮና ስነ-ልቦና ራሳቸውን የሚያጎለብቱባቸዉ እንዲሁም በእረፍት ጊዜያቸው የሚዝናኑባቸዉ ቦታዎች እንዲሆኑ ማስቻል በማስፈለጉ፤

የወጣቶችና ስፖርት ቢሮ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 74/2014 አንቀጽ 15 ንዑስ-አንቀፅ (2) ተራ ፊደል (ሠ) መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## Directive No. 107//2022
## Addis Ababa City Government Youth Personality Enrichment Centers Administration and Service Delivery

**Whereas,** it has been considered that the youth personality enrichment centers have paramount importance to enable the youth to actively participate in the overall development endeavors of the city and the nation as well as to help them benefit from the thereof through tackling the various social, economic, and political problems of the youths of the Addis Ababa City government;

**Whereas,** it has been found necessary to enable the youth personality enrichment centers to provide services in an effective, sustainable manner and through the participation of the youth so as to make the centers conducive for the youth to develop themselves physically, mentally, and psychologically as well as entertain themselves in their leisure time;

**Now, therefore,** in accordance with letter (E) of Sub-Article (2) of Article 15 of the Addis Ababa City Government Executive Organs Establishment Proclamation number 74/2021, the Youth and Sports Bureau has issued this directive.

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የወጣት ስብዕና መገንቢያ ማዕከላት አስተዳደርና አገልግሎት አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 107/2014" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1/ **"ቢሮ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ማለት ነው፤

2/ **"ወጣት"** ማለት ማንኛውም ከ 15-29 ዓመት የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኝ ሰው ማለት ነው፤

3/ **"ጽህፈት ቤት"** ማለት በክፍለ-ከተማና በወረዳ አስተዳደር የሚገኙ የወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ጽህፈት ቤት ነው፤

4/ **"ቦርድ"** ማለት የወጣቶች ስብዕና መገንቢያ ማዕከላትን በበላይነት የሚመራ አካል ነው፤

5/ **"የወጣት ስብዕና መገንቢያ ማዕከል"** ማለት ለወጣቶች አዕምሯዊ፣ ሥነ-ልቦናዊና አካላዊ ዕድገት አጋዥ የሆኑ አገልግሎቶችን የሚሰጥ ተቋም ነዉ፤

6/ **"ደንብ"** ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የወጣቶች ስብዕና መገንቢያ ማዕከላት ደንብ ነው፤

7/ **"መመሪያ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ ያጸደቀው የወጣት ስብዕና መገንቢያ ማዕከላት መተዳደሪያ ደንብ ለማስፈጸም የወጣ ዝርዝር አፈጻጸም መመሪያ ማለት ነው፤

8/ **"ፕሮሰስ ካውንስል"** ማለት የወጣቶች ስብዕና መገንቢያ ማዕከላት ዋና ዋና የስራ ክፍሎች ሰራተኞችን የያዘ የማኔጅመንት ኮሚቴ ማለት ነው፡፡

## Part One

## Generals

1. **Short Title**

This directive may be cited as: **"**The Addis Ababa City Government Youth personality Enrichment Centers Administration and Service Delivery Directive number 107/2022**"**

2. **Definition**

In this directive, unless the context requires otherwise:

1. **"Bureau"** means the Addis Ababa City Government Youth and Sports Bureau;
2. **"Youth"** means any person with the age range of 15 to 29;
3. **"Office"** means the youth and sports offices that are found at sub-city and woreda levels;
4. **"Board"** means an organ that superiorly leads the youth personality enrichment centers;
5. **"Youth Personality Enrichment Centers"** means an institution that provides services to help the mental, psychological, and physical development of the youth;
6. **"Regulation"** means the Addis Ababa City Government Youth Personality Enrichment Centers Regulation;
7. **"Directive"** means the detailed directive issued for the implementation of the youth personality enrichment centers Regulation that was approved by the Cabinet of the Addis Ababa City Government;
8. **"Process Council"** means a management committee that comprises employees of the major departments of the youth personality enrichment centers.

**3. *የተፈጻሚነት ወሰን***

*ይህ መመሪያ በከተማው የወጣቶች ስብዕና መገንቢያ ማዕከላት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡*

**4. *የመመሪያው ዓላማ***

*በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውስጥ የሚገነቡና በአስተዳደሩ ባለቤትነት የሚንቀሳቀሱ የወጣት ስብዕና መገንቢያ ማዕከላት ተገቢውን አገልግሎት እንዲሰጡ በማድረግ የወጣት ስብዕና መገንቢያ ማዕከላቱ ወጣቶች ጤናቸው የተጠበቀ፣ በአካልና በአዕምሮ የዳበሩ ብቁ ዜጎችን እንዲያፈሩ የሚያስችል ስርዓት መዘርጋት ነው፡፡*

## *ክፍል ሁለት*

## *ለወጣቶች የሚሰጡ የአገልግሎት አሰጣጥ መርሆዎችና የአገልግሎት አይነቶች*

**5. *ለወጣቶች የሚሰጡ የአገልግሎት አሰጣጥ መርሆዎች***

*የወጣት ስብዕና መገንቢያ ማዕከላት ለወጣቶች የሚሰጡትን አገልግሎት ተገቢውን እውቅና እንዲያገኙ የሚከተሉትን መርሆዎች መከተል አለባቸው፡-*

1/ *ከተጠቃሚው ጋር በሚያወጧቸው የፕሮግራም ግቦችና አገልግሎቶች አጋርነት የመፍጠር፤*

2/ *የሚሰጡ አገልግሎቶች በተጠቃሚው ፍላጎት ላይ ያተኮረ ማድረግ፤*

3/ *የአገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ዘርፈ-ብዙ የሙያ መስክ ያካተተ ማድረግ፤*

4/ *ብቁ ባለሙያዎችን መመደብ፤*

5/ *የሚሰጡ አገልግሎቶችን ለወጣቶች ተደራሽ ማድረግ፤*

**3. Scope of Application**

This directive shall be applicable to youth personality enrichment centers of the city.

**4. The objective of the Directive**

To establish a system that enables to produce of healthy, physically fit, and mentally developed youths so as to have competent citizens through making sure that the youth personality enrichment centers that are being built in the Addis Ababa City government and under the ownership of the city administration provide relevant services.

## Part Two

## Principles of Service Delivery for the Youth and Types of Services

**5. Principles of Service Delivery for the Youth**

Youth personality enrichment centers must adhere to the following principles in order to get the relevant recognition for the services they provide for the youth:

1/ create a partnership with the users in designing goals for the programs and services;

2/ make sure that the services to be provided are focused on the needs of the users;

3/ make sure that the service provision process includes multifaceted professions;

4/ assign capable professionals;

5/ ensure the rendered services are accessible to the youths;

6/ የአገልግሎቱን ስኬታማነት በመለካት የተገኘውን ውጤት በተጠቃሚው የሚመዘንበት የተጠያቂነት አሰራር ማስፈን፤

7/ የወጣቱን ተሳትፎና ባለቤትነት ማረጋገጥ፤

8/ የሴቶችንና የአካል ጉዳተኛ ወጣቶችን እኩል ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ናቸው፤

9/ ለተደራጁ ስራ ፈላጊ ወጣቶች የሥራ ዕድል መፍጠሪያ ማድረግ፡፡

6. <u>የቤተ-መጽሐፍት አገልግሎት</u>

1/ የቤተ-መጽሃፍቱ አባል የሚሆኑና የፕሮሰስ ካውንስሉ በሚያወጣው የመጽሃፍ ማዋስ ስርዓት መሰረት ተገልጋዮች ለአንድ ሳምንት ያክል መዋስ ይችላሉ፤

2/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 መሰረት መጽሃፍ የተዋሰ ሰው ከተወሰነው ጊዜ ውጪ ቢያቆይ ለመጀመሪያው አንድ ሳምንት በቀን ሁለት ብር፤ ከአንድ ሳምንት በላይ ሲቆይ በቀን አምስት ብር የቅጣት ክፍያ የሚከፍል ሆኖ መጽሐፉ ካልተመለሰ እንደጠፋ ተቆጥሮ የመጽሐፉ ዋጋ ሁለት እጥፍ ዋሱ እንዲከፍል ይደረጋል፤

3/ ተገልጋይ መጽሃፍ ቢያበላሽ፣ ቢቀድ ወይም ተውሶ ቢጠፋበት የመጽሃፉን ዋጋ ሁለት እጥፍ መክፈል አለበት፤ ማዕከሉ ተመሳሳዩን ገዝቶ እንዲተካ ይደረጋል፡፡

7. <u>የማዕከሉ ቤተ-መጻህፍት ስለሚሰጣቸው አገልግሎቶች</u>

1/ የተለያዩ ትምህርታዊ መጽሃፍቶች፣ ልቦለዶች፣ ዲክሽነሪዎችና ኢንሳይክሎፒዲያዎች፤

2/ ጋዜጦች፣ መጽሄቶች፣ በራሪ ጽሁፎች ማዘጋጀት፤

6/ establish a user-led accountability procedure by evaluating the successfulness of the services through evaluating the obtained results;

7/ ensure the participation and ownership of the youth;

8/ ensure equal access for women and youths with physical disabilities;

9/ Creating job opportunities for those organized youths that are seeking jobs.

6. **<u>Library Service</u>**

1/ customers, who are going to be members of the library and based on the book borrowing system to be set by the process council, may borrow books for one week;

2/ pursuant to Sub-Article 1 of this Article, the person who borrowed a book and fails to return it in the specified time will pay birr two per day for the first week, and birr five per day for more than one week; and if the book is not returned, it shall be considered as a lost one and the delegate shall pay two folds of the price of the book;

3/ a customer shall pay two folds of the price of the book if it is damaged, thorn apart, or lost; the center shall buy the book and replace it.

7. **<u>Services provided by the Library of the Center</u>**

1/ various textbooks, fictions, dictionaries, and encyclopedias;

2/ newspapers, magazines, preparing brochures;

3/ የተለያዩ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ማቅረብ፤

4/ የምስልና የድምጽ ትምህርታዊ ካሴቶች፣ ሲዲዎችና ቪዲዮች፤

5/ የተለያዩ ካርታዎች፤

6/ ፎቶግራፎችና ታሪካዊ ምስሎች፤

7/ ወጣት ተኮር ጤና-ነክ እና ሌሎች ጤና-ነክ መረጃዎች፤

8/ ዲጅታል መጽሃፍቶች፤ እና

9/ የብሬል ጽሁፎች

ይኖሩታል፡፡

## 8. <u>የቤተ-መጽሃፍት ተገልጋይ ግዴታዎች</u>

ማንኛውም ሰው በቤተ-መፅሃፍቱ ሲጠቀም የሚከተሉትን ግዴታዎች ማክበር አለበት፡-

1/ የቤተ-መጻህፍቱን ጸጥታ ማክበርና ማስከበር፤

2/ የተዋሱትን መጽሃፍት በጊዜው መመለስ፤

3/ የተጠቀሙበትን መጽሃፍት ወደ ቦታው መመለስ፤

4/ የሞባይል ስልክ አለመጠቀም፤

5/ ኮምፒዉተሮችንና መጽሃፍቶችን በጥንቃቄ የመያዝና የመጠቀም፤

6/ የቡድን ውይይት አለማድረግ፤ እና

7/ ቤተ-መጽሃፍቱ የሚያወጣውን ደንብና መመሪያ መከተል አለበት፡፡

## 9. <u>የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ አገልግሎት</u>

1/ ማዕከሉ የኢንተርኔት፣ የፎቶ ኮፒ፣ የመጠረዝ፣ የዋይፋይ፣ ማሸግ፣ የፅህፈት፣ የህትመት እና ሌሎች አገልግሎቶችን ይሰጣል፤ አገልግሎቶችን ለማግኘት

3/ providing various Proclamations, Regulations, and directives;

4/ audio and video educational cassettes, CDs, and videos;

5/ various maps;

6/ photographs and historical images;

7/ youth-focused health-related and other information;

8/ digital books, and

9/ Braille writings

## 8. <u>Obligations of Customers of the Library</u>

Any individual should obey the following obligations while using the library:

1/ maintain silence in the library and respect the thereof;

2/ return borrowed books on time;

3/ place the books properly;

4/ not using mobile phones;

5/ carefully handle and use computers and books;

6/ avoid group discussions;

7/ follow the rules and regulations set by the library.

## 9. <u>Information Communication Technology Services</u>

1/ the center provides internet, photocopy, binding, wifi, laminating, writing, printing, and other services; the process council of the center may determine an

ተመጣጣኝ ዋጋ የማዕከሉ ፕሮሰስ ካውንስል ሊወሰን ይችላል፤

2/ የሀገሪቱን እሴቶች የሚጻረሩ ወሲብ-ነክ ምስሎችና መልዕክቶችን መጠቀም፤ ፖለቲካዊ፣ ሀይማኖታዊ፣ ዘርና ባህልን የሚጻረሩ ድርጊቶችን መመልከትና መላላክ የተከለከለ ነው፤

3/ የኢንተርኔት ዋጋ ጭማሪ ወይም ቅናሽ የሚያሳይ ሲሆን እንደ አስፈላጊነቱ በፕሮሰስ ካውንስሉ ሲታመንበት ክፍያው ሊከለስ ይችላል፡፡

10. <u>ወጣት ተኮር የሥነ-ተዋልዶ ጤና አገልግሎት</u>

በወጣት ስብዕና መገንቢያ ማዕከል የሚከተሉት የስነ-ተዋልዶ አገልግሎቶች ይሰጣሉ፡-

1/ የስነ-ተዋልዶ ጤና መረጃና ምክር አገልግሎት መስጠት፤

2/ የቤተሰብ ምጣኔ መረጃ የምክክር ወይም ካውንስሊንግ፣ ያልተፈለገ እርግዝናን የመከላለከል ዘዴዎችን ማስተማር፤

3/ ኮንዶምን ማስተዋወቅና ስርጭት ተግባር ማከናወን፤

4/ የእርግዝና እና የኤች.አይ.ቪ./ኤድስ የምክርና የምርመራ አገልግሎት መስጠት፤

5/ በሚፈጠሩ ወቅታዊ በሽታዎችን ከሚመለከተው አካል ጋር በመተባበር በዘመቻ የመከላከል ስራ ማከናወን፤

6/ የሰውነት ክብደትን፣ የደም ግፊትን፣ የደም የስኳር መጠንን የመለካት ሥራዎችን እና መሰል አገልግሎቶችን ማከናወን፤

affordable process for having the services;

2/ using pornographic images and messages, as well as watching and exchanging political, religious, racial, and cultural activities that violate the values of the country are prohibited;

3/ when the price of the internet service shows an increase or decrease, the fee might be revised as may be necessary when such is accepted by the process council.

10. **<u>Youth-focused Reproductive health Services</u>**

The following reproductive health services are offered at the youth personality enrichment centers:

1/ providing reproductive health information and counseling services;

2/ family planning information, counseling, providing lessons that help to prevent unwanted pregnancy;

3/ promote the use of condom and distribution activities;

4/ providing pregnancy and HIV/AIDS counseling and testing services;

5/ carry out prevention activities on accidental diseases in collaboration with the relevant organs;

6/ undertake measuring of weight, blood pressure, blood sugar level, and other similar activities;

7/ የመጀመሪያ ህክምና እርዳታ አገልግሎት መስጠት፤

8/ በአካባቢያቸው ከሚገኙ ጤና ጣቢያ ወይም ሆስፒታል ጋር በቅንጅት ይሰራሉ፤ ከአቅማቸው በላይ የሆነውን ሪፈር ያደርጋሉ፤ ባለሙያዎችን በመጋበዝ ግንዛቤ እንዲፈጠር ያደርጋሉ፤

9/ በአስተዳደሩ ጤና ቢሮ የሚተላለፍ ወቅታዊ ጤና-ነክ ጉዳዮችን በመከታተል ተግባራዊ ያደርጋሉ፤

10/ እነዚህን ከላይ የተዘረዘሩትን ተግባራት የሚያከናውኑ ባለሙያዎች በጤና ቢሮ የተረጋገጠ የሙያ ብቃት ያላቸው ወይም እውቅና ያላቸው ሊሆኑ ይገባል፡፡

**11. <u>የጤና አገልግሎት ሰጪ ባህሪያት</u>**

**ሀ. የማዕከሉ የጤና አገልግሎት አሰጣጥ ባህሪ/ሁኔታ**

1/ ለወጣቶች የአገልግሎት መስጫ ጊዜን ምቹ ማድረግ፤

2/ የአገልግሎት መስጫ ክፍሎችን ለወጣቶች ምቹ ማድረግ፤

3/ ብቃት ባላቸው ባለሙያዎች አገልግሎቱን መስጠት፤

4/ በቂ የቁሳቁስና የመድሃኒት አቅርቦት እንዲኖር ማድረግ፤

5/ ወጣቶችን አሳታፊ በሆነና የአካል ጉዳተኛ ወጣቶችን ፍላጎት ባገናዘበ መንገድ አገልግሎት መስጠት፤

6/ የሪፈራል አገልግሎት የአሰራር ስርዓት መዘርጋት፤

7/ የወጣቶችን የጤና ሁኔታ ክትትል ማድረግ፤

7/ provide first aid services;

8/ work in collaboration with health centers or hospitals that are found around their vicinity; refer cases that are beyond their level; create awareness by inviting experts;

9/ follow up up-to-date health-related issues transmitted by the health bureau of the city administration, and implement the thereof;

10/ the professional that will carry out the above stated activities should have a professional competence or recognition that was accredited by the health bureau.

**11. <u>Characteristics of health Service Providers</u>**

**A. Characteristics/Conditions of the Health Service Provision of the Center**

1. ensure that the service provision time is convenient for the youth;
2. make sure that the service provision rooms are conducive for the youth;
3. provide the service with competent professionals;
4. ensure the presence of adequate supply of materials and medicines;
5. provide services with the participation of the youths and by considering the interests of youths with physical disabilities;
6. establish a procedure for providing referral service;
7. follow up the health condition of the youths;

ለ. የማዕከሉ የጤና የባለሙያዎች ባህሪ/ሁኔታ

1/ የግል ሚስጥር መጠበቅ፤

2/ ለወጣቶች ክብር መስጠት፤

3/ የወጣቶችን ፍላጎት ታሳቢ ባደረገ መልኩና አሳታፊ በሆነ መንገድ አገልግሎቱን መስጠት፤

4/ በቂ ጊዜ ለተገልጋዮች መስጠት፤

5/ የግል ብቃትና ክህሎትን በየጊዜው ማሳደግ፤

12. <u>ወጣት ተኮር የሥልጠና አገልግሎት</u>

1/ በወጣት ስብዕና መገንቢያ ማዕከሉ የተለያዩ የወጣቶችን ፍላጎት መሰረት ያደረጉ ክህሎትና አመለካከት የሚያጎለብቱ ስልጠናዎች ይሰጣሉ፡፡

2/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ-አንቀፅ 1 መሰረት የሚሰጡት ስልጠናዎች የሚከተሉትን ያካተተ ይሆናል፡-

ሀ) የስራ ፈጠራ ክህሎት ስልጠና፤

ለ) የሀብት አሰባሰብና ፕሮጀክት አቀራረጽ ክህሎት ስልጠና፤

ሐ) የንግድ ንድፈ-ሃሳብ ወይም ቢዝነስ ፕላን አቀራረጽ ክህሎት ስልጠና፤

መ) የኤች.አይ.ቪ/ኤድስና የስነ-ተዋልዶ ጤና አጠባበቅ ስልጠና፤

ሠ) የበጎ ፍቃድ አገልግሎት አሰጣጥ ስልጠና፤

ረ) የህይወት ክህሎት ስልጠና፤

ሰ) የአመራር ክህሎት ስልጠና፤

ሸ) የጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን መከላከል ስልጠና፤

**B. Characteristics/Conditions of the Health Professional of the Center**

1. confidentiality;
2. respecting the youth;
3. providing the services by considering the interests of the youths and participating the thereof;
4. give enough time for customers;
5. develop once own competence and skills progressively;

**12. <u>Youth-centered Training Services</u>**

1/ training that are based on the various needs of the youth will be given in the youth personality enrichment centers so as to develop the skills and attitudes of the youth;

2/ the training that will be provided in accordance with Sub-Article 1 of this Article shall include the following:

a) job creation skills training;

b) resource mobilization and project designing skills training;

c) business proposal or business plan designing skills training;

d) HIV/AIDS and reproductive health care training;

e) voluntary service provision training;

f) life skills training;

g) leadership training;

h) training to prevent harmful traditional practices;

ቀ) ህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር መከላከል ስልጠና፤

በ) የአደንዛዥ እጽ ተጠቃሚነት እና ዝውውር መከላከል ስልጠና፤

ተ) የመጀመሪያ ህክምና እርዳታ አሰጣጥ ክህሎት ስልጠና፤

ቸ) የተለያዩ ስፖርታዊ ስልጠናዎችንና ሌሎች አስፈላጊ የክህሎት ስልጠናዎችንም በማካተትና በማዘጋጀት ስልጠናዎች ይሰጣሉ፡፡

i) training on prevention of human trafficking;

j) drug use and trafficking prevention training;

k) training on the provision of first aid;

l) providing various sports-related training and includes and preparing other necessary skill training.

13. <u>የኮምፒውተርና ቴክኖሎጂ ስልጠናዎች</u>

1/ ወጣቶች በማዕከሉ የኮምፒውተርና ተያያዥነት ያላቸው የቴክኖሎጂ ስልጠናዎች እንዲያገኙ ይደረጋል፤

2/ የአገልግሎቱ ዋጋ ተመጣጣኝ ክፍያና የሰርተፍኬት አሰጣጥ አገልግሎት በሚዘጋጀው ስታንዳርድና በአሰራሩ ፈቃድ መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል፤

3/ የሚሰጠው ስልጠና የክፍያ መጠን እንደ ኮርሱ ሁኔታ በፕሮሰስ ካውንስሉ ይወሰናል፡፡

4/ በዚህ አንቀፅ መሰረት በማዕከሉ የሚሰጡ ስልጠናዎች የሚከተሉትን ያካትታል፡-

ሀ) መሰረታዊ የኮምፒውተር አጠቃቀም ክህሎት ስልጠና፤

ለ) የኔትወርክ ዝርጋታ ክህሎት ስልጠና፤

ሐ) ሶፍትዌር የማበልጸግ ክህሎት ስልጠና፤

መ) የታይፒንግ ክህሎት ስልጠና፤

ሠ) የ Peachtree ክህሎት ስልጠና፤

13. **<u>Computer and Technology Training</u>**

1/ make sure that the youths will be provided with computer and other technology related training in the center;

2/ the training shall be provided with an affordable fee, and the provision of certificate for the thereof will be implemented as per the standards and procedures to be established;

3/ the amount of fee for the offered training will be specified by the process council as per the condition of the training;

4/ pursuant to this Article, the training to be provided in the center shall include the following:

A. basic computer utilization skills training;

B. network installation skills training;

C. software development skills training;

D. typing skills training;

E. Peachtree skills training;

ረ) የጃቫና C++programming ክህሎት ስልጠና፤ እና

ሰ) የቢሮና ቀላል ማሽኖች አጠቃቀምና ጥገና፣ ኤሌክትሮኒክስ፣ ፎቶኮፒ፣ ፕሪንት፣ ስካን፣ ፋክስ፣ ባይንድ፣ ላሚኔት እና የመሳሰሉ ሌሎች የወጣቶችን ክህሎት የሚያዳብሩ አጫጭር የሙያና የቴክኖሎጂ ስልጠናዎች ይሰጣሉ፡፡

**14. <u>የኪነ-ጥበብ ተሰጥዖን የሚያዳብሩ ስልጠናዎች</u>**

1/ የቲያትር ድርሰት አጻጻፍ እና ትወና ክህሎት ስልጠና፤

2/ የባህላዊ እና ዘመናዊ ዳንስ ክህሎት ስልጠና፤

3/ የድምጽ ተሰጥዖ ክህሎት ስልጠና፤

4/ የባህላዊ እና ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች አጠቃቀም ክህሎት ስልጠና፤

5/ የፊልም ድርሰት አፃፃፍ ክህሎት ስልጠና፤

6/ የፎቶና ቪዲዮ ኤዲቲንግ ክህሎት ስልጠና፤

7/ የፊልምና ቲያትር ዳይሬክቲንግ ክህሎት ስልጠና፤

8/ የመድረክ አመራር ክህሎት ስልጠና፤

9/ የቴሌቭዥን ፕሮግራም አመራር ክህሎት ስልጠና፤

10/ የሬዲዮ ፕሮግራም አመራር ክህሎት ስልጠና፤ እና

11/ የማስታወቂያ ስራ ክህሎት ስልጠና እና የመሳሰሉትን ከላይ ከተጠቀሱት ሙያዎች ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ሌሎች አጫጭር ስልጠናዎች ይሰጣሉ፡፡

F. Java and C++ programming skills training; and

G. utilization and maintenance training of office and simple machines; and provides short-term vocational and technology-based training related to electronics, photocopying, printing, scanning, fax, binding, laminating, and similar others that develop the skills of the youths.

**14. <u>Training intended to Develop Artistic Talents</u>**

1/ theatrical creative writing and acting skills training;

2/ traditional and contemporary dancing skills training;

3/ vocal skills training;

4/ training on the use of traditional and modern musical instruments;

5/ film scripts writing skills training;

6/ photo and video editing skills training;

7/ film and theatre directing skill training;

8/ stage leading skill training;

9/ television programs presentation skill training;

10/ radio programs presentation skill training;

11/ promotion activities skill training; and provides other short training related to the above-stated professions.

**15. የቋንቋ ክህሎት ስልጠናዎች**

1/ የምልክት ቋንቋ ክህሎት ስልጠና፤

2/ የሀገር ውስጥ ቋንቋዎች ክህሎት ስልጠና፤

3/ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ክህሎት ስልጠና፤

4/ የፈረንሳይኛ ቋንቋ ክህሎት ስልጠና፤

5/ የቻይንኛ ቋንቋ ክህሎት ስልጠና፤ እና

6/ አረብኛ እና የመሳሰሉትን ቋንቋዎች የክህሎት ስልጠና በተግባር እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡

**16. የስልጠና ቅድመ-ሁኔታዎች**

በወጣት ስብዕና መገንቢያ ማዕካለት ውስጥ ወጣቶችን ይጠቅማሉ ተብለው የሚዘጋጁ ስልጠናዎች ሁሉ የሚከተሉትን ቅድመ-ሁኔታዎች ማሟላት ይኖርባቸዋል፡-

1/ ስልጠናዎቹ በወጣቶች ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ላይ የተመሰረቱ መሆን አለባቸው፤

2/ ስልጠናዎቹ ሁሉ የወጣቶችን የእድሜ እርከን ያገናዘቡ መሆን አለባቸው፤

3/ ስልጠናዎቹ የወጣቶችን አመለካከት፣ ስራ ለመፍጠ፣ር ገቢ ለማስገኘት፣ ድህነትን ለመቅረፍ የሚያስችሉ፣ ጥገኛ አስተሳሰቦችኝ ለማስወገድ የሚያስችሉና የባህሪይ ለውጥ የሚያመጡ መሆን አለባቸው፤

4/ ሰልጣኞች ስልጠናውን ሲያጠናቅቁ የምስክር ወረቀት የማግኘት መብት አላቸው፤

5/ አሰልጣኞች በትምህርት ዝግጅትና የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሊኖራቸው ይገባል፤

**15. Training on Language Skills**

1/ sign language skill training;

2/ local languages skill training;

3/ English language skill training;

4/ French language skill training;

5/ Chinese language skill training;

6/ Arabic and other languages skills training will be provided practically.

**16. Pre-requisites for a Training**

All the training that are prepared in the youth personality enrichment centers and intended to benefit the youth shall fulfill the following pre-conditions:

1/ training should be based on the need assessment findings of the youth;

2/ all training should consider the age level of the youth;

3/ the training should be aimed at changing the attitude of the youth, creating job opportunities, generating income, reducing poverty, avoiding unfavorable ideas, and resulting behavioral change;

4/ trainees have the right to get a certificate upon the completion of the training;

5/ trainers should have a certificate on their educational qualification and professional competence;

6/ አሰልጣኞች በስነ-ምግባር የታነጹና ለወጣቶች ምሳሌ መሆን አለባቸው፤

7/ የስልጠና አሰጣጥ በሰልጣኞች በመገምገም ማሻሻያ ሊደረግባቸው የሚችልበት አሰራር ሊኖር ይገባል፤

8/ እንደ አስፈላጊነቱ አሰልጣኝ ከወጣት አደረጃጀቶች፣ ከወጣቶች ክበባት ጥምረት፣ ከበጎ ፍቃደኛ ወጣቶች፣ ከወጣቶች በጎ ፍቃድ ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት፣ ከወጣቶች በጎ ፍቃድ ማስተባበሪያ ቢሮ ሰራተኞች፣ ከተጋባዥ እንግዶች፣ ከሌሎች ተቋማት ወይም ከማዕከሉ አስተዳደር ጋር በመወሰን የፕሮሰስ ካውንስሉ በመወሰን ቅጥር ሊካሄድ ይችላል፡፡

6/ trainers should be well behaved and exemplary for the youth;

7/ there might be an established procedure to evaluate the training scheme by trainees and improve the thereof;

8/ the process council in consultation with the management of the center may hire trainers from youth organizations, youth clubs, youth volunteers, youth volunteers coordination office, employees of the youth volunteers coordination office, invited guests, and other institutions as may be necessary.

## 17. የሥነ-ልቦና እና የምክር አገልግሎት

1/ ወጣቶችን ከተለያዩ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ቀውሶች ማለትም ከመጤ ጎጂ ልማዶች፣ በአደንዛዥ ዕጽ አማካኝነት ከሚከሰቱ ችግሮች፣ ስራ አጥነት ለመታደግ ወጣቶች በሚያነሱዋቸው ጉዳዮች ላይ የማማከር አገልግሎት በመስጠት ከተለያዩ ማህበራዊ ችግሮች እንዲላቀቁ ለመስራት ማዕከሉ የሥነ-ልቦና እና የምክር አገልግሎት ይሰጣል፤

2/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 መሰረት የሚሰጠው የማማከር አገልግሎቱ በፍቃደኝነት ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት፡፡

## 17. Psychological and Counseling Service

1/ the center shall provide psychological and counseling services based on issues raise by the youth to address the various social problems of the youth and help the youth to deal with the different social and economic crises such as external harmful practices, problems related to drugs, and unemployment.

2/ the counseling service to be provided pursuant to Sub-Article 1 of this Article should be voluntary.

18. <u>የሥነ-ልቦና እና የምክር አገልግሎት ሰጪ ባህሪያት</u>

**ሀ. የማዕከሉ የሥነ-ልቦና እና የምክር አገልግሎት አሰጣጥ ባህሪ/ሁኔታ**

1/ ለወጣቶች የአገልግሎት መስጫ ጊዜን ምቹ ማድረግ፤

2/ የአገልግሎት መስጫ ክፍሎችን ለወጣቶች ምቹ ማድረግ፤

3/ ብቃት ባላቸው ባለሙያዎች አገልግሎቱን መስጠት፤

4/ በቂ የቁሳቁስና የመድሃኒት አቀርቦት እንዲኖር ማድረግ፤

5/ ወጣቶችን አሳታፊ በሆነ መንገድ አገልግሎት መስጠት፤

6/ የወጣቶችን ስነ-ልቦናዊ ሁኔታ ክትትል ማድረግ፤

**ለ. የማዕከሉ የሥነ-ልቦና ባለሙያዎች ባህሪ/ሁኔታ**

1/ የግል ሚስጥር መጠበቅ፤

2/ ለወጣቶች ክብር መስጠት፤

3/ በቂ ጊዜ ለተገልጋዮች መስጠት፤

4/ በቂ ክትትል ማድረግ፤

5/ ወጣቶችን አሳታፊ በሆነ መንገድ አገልግሎቱ መስጠት፤

6/ የግል ብቃትና ክህሎትን በየጊዜው ማሳደግ፤

19. <u>የካፍቴሪያና የሬስቶራንት አገልግሎት</u>

1/ የወጣት ስብዕና መገንቢያ ማዕከሉ ከሚሰጣቸው አገልግሎቶች መካከል የካፌ እና ሬስቶራንት አገልግሎት ይሰጣል፤

2/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ-አንቀፅ 1 መሰረት የሚቀርበው አገልግሎት የአልኮል መጠጦችን ማቅረብ፣ ጫት መቃምና

**18. <u>Characteristics of Psychological and Counseling Service Provider</u>**

**A. Characteristics/Conditions of the Psychological and Counseling Service Provision of the Center**

1/ ensure that the service provision time is convenient for the youth;

2/ make sure that the service provision rooms are conducive for the youth;

3/ provide the service with competent professionals;

4/ ensure the presence of adequate supply of materials and medicines;

5/ provide services in a way that participate the youths;

6/ follow up the psychological condition of the youths;

**B. Characteristics/Conditions of the Psychologists of the Center**

1/ confidentiality;

2/ respecting the youth;

3/ provide enough time for the customers;

4/ make proper follow ups;

5/ providing the service with the participation of the youths;

6/ develop once own competence and skills progressively;

**19. <u>Cafeteria and Restaurant Service</u>**

1/ the youth personality enrichment center shall provide cafeteria and restaurant service;

2/ the services provided according to Sub-Article 1 of this Article will not allow serving alcohol beverages, using and

ማስቃም፣ ሌሎች አደንዛዥ እጾችን መጠቀም አይፈቀድም፤

3/ የካፍቴሪያው አጠቃቀምና አስተዳደር በተመለከተ ተደራጅተው ለሚመጡ ወጣቶች ወይም በስራ ዕድል ፈጠራና ኢንተርፕራይዞችን ማደራጀት ጽህፈት ቤት የተደራጁ ወጣቶች በጨረታ ተወዳድረው ለአሸናፊው በኪራይ የሚሰጥ ሆኖ አሸናፊው አካል በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የግዢ መመሪያ መሰረት ከማዕከሉ አስተዳደር ጋር ውል ተዋውሎ ስራውን ይጀምራል፤

4/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ-አንቀፅ 3 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ለጨረታ የቀረበ አካል ከሌለ ማዕከሉ በራሱ አቅም የሚያስተዳድር ይሆናል፤

5/ የአገልግሎቱ ክፍያ መጠን የተገልጋዩን የመግዛት አቅም ያማከለ እንዲሆን በፕሮሰስ ካዉንስሉ ተወስኖ ከአሸናፊው ጋር ስምምነት መደረግ ይኖርበታል፤

6/ የካፍቴሪያው አገልግሎት በጨረታ ተደራጅተው የአሸነፉት ወጣቶች በማዕከሉ አዳራሽ የሚካሄዱትን ማንኛውም የስብሰባና ሌሎች ፕሮግራሞች የመስተንግዶ አገልግሎት ቅድሚያ ያገኛሉ፡፡

7/ የካፌ እና ሬስቶራንቱ ውል በየስድስት ወሩ የሚታደስ ውል ሆኖ እስከ አምስት አመት ዉላቸዉን እያደሱ ሊቆዩ የሚችሉ ሲሆን አምስት ዓመት ካለቀ በኋላ ግን በማሰናበት በጨረታ ለሌላ አሸናፊ ማህበር የሚሰጥ ይሆናል፤

serving ‘chat’, and using other drugs;

3/ regarding the utilization and administration of the cafeteria, it shall be transferred through a lease to those organized youths or youths organized by the job creation and enterprise coordination office through bidding, and the winner shall enter into a contract with the administration of the center as per the procurement directive of the Addis Ababa City Government; and starts its service;

4/ without prejudice to the provisions of Sub-Article 3 of this Article, if there is no entity involved in the bidding process, the center shall run the cafeteria on its own;

5/ the process council shall decide the service fees and reach an agreement with the winner in order to make the amount of the service charges affordable for the customers;

6/ the organized youths that won the bidding of the cafeteria service shall get priority for reception services to be provided for any meetings and other events to be held at the center’s hall;

7/ the contract of the cafeteria and restaurant shall be renewed every six months, and it will be effective up to five years in such manner; but after five years, the existing contract shall be terminated and the service will be given to another association through bidding;

8/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ-አንቀፅ 7 የተደነገገው ቢኖርም በተወሰነው ጊዜ ውስጥ የማዕከሉን ጤናማ አገልግሎት የሚጻረር ወይም የሚያጎድፍ ወይም የግል ጥቅምን ለማዳበር እንቅስቃሴ የሚያደርጉና ከውል ውጪ የሚከናወኑ ድርጊቶች ቢኖሩ የማዕከሉ አስተዳደር ውል ሊያቋርጥ ይችላል፤

9/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ-አንቀፅ 8 መሰረት የሚወሰደው እርምጃ የሚከተሉትን መከተል አለበት፡-

ሀ) በመጀመሪያ በቃል ማስጠንቀቂያ መስጠት፤

ለ) በጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል፤

ሐ) የውል ጊዜው ሳይጠናቀቅ በፊት ማሰናበት፤

መ) ውል ተቀባዩ ድርጊቱን ካላሻሻለ ለማዕከሉ የውሉ ዘመኑ ሳይደርስ ካፍቴሪያውን ያለ ምንም ቀሪ ገንዘብ ተመላሽ ውሉን በማቋረጥ ለሌላ የማስተላለፍ ስልጣን እንዳለው በኮንትራት ውል ስምምነቱ ውስጥ መጠቀስ አለበት፤

ሠ) የጥፋቱ ክብደት ተመዝኖ ተከራዩ እንደ ድርጊቱ ክብደት ካለምንም ማስጠንቀቂያ ሊሰናበት ይችላል፡፡ ይህም በፕሮሰስ ካውንስል ሲታመንበት ተግባራዊ ይሆናል፡፡

**20. <u>የቤት ውስጥ ጨዋታዎች አገልግሎት</u>**

1/ ወጣቶች በማዕከላቱ የተሟላ የቤት ውስጥ ስፓርታዊና አዝናኝ አገልግሎቶችን ያገኛሉ፤

8/ notwithstanding to the provisions of Sub-Article 7 of this Article, the management of the center may terminate the contract within the specified period if there are activities that violate or harms the regular and healthy services of the center or tries to unlawfully gain one own personal interest and carries out activities in contrary to the contract;

9/ the measures to be taken pursuant to Sub-Article 8 of this Article should follow the following things:

a) first, there should be an oral warning;

b) written warning;

c) dismissal before the end of the contract period;

d) if the party that commits the offence does not improve the wrongdoings, it must be stated in the contract that the center has the right to take the cafeteria back before the end of the contract period without any back payment and has the power to transfer it to another party;

e) the tenant may be dismissed without any given notice through examining the severity of the offense; such will be applied upon the consent of the process council.

**20. <u>Indoor Games Service</u>**

1/ the youth will get a full range of indoor games sports and entertainment services in the center;

2/ የፑል፣ ጆተኒ፣ ፕሌይ ስቴሽን እና ዲ.ኤስ.ቴቪ. አገልግሎቶች ተደራጅተዉ ጨረታ ለአሸነፉ ወጣቶች የሚሰጥ ይሆናል፤

3/ ክፍያ የሚደረግባቸዉ የቤት ዉስጥ ጨዋታዎች የክፍያ መጠን የወጣቶችን አቅም ባገናዘበ መልኩ በማዕከላቱ የፕሮሰስ ካዉንስል የሚወሰን ይሆናል፡፡

4/ መስመራቸው በኮንትራት በግዢ ከሆነ ለምሳሌ የዲ.ኤስ.ቲቪ. እና የፕሌይ ስቴሽን በተለይም ለእግር ኳስ፣ ለአትሌቲክስና ሌሎች የመዝናኛ ፕሮግራሞች ብቻ ለማግኘት በሰው ብር 5.00 (አምስት ብር) መክፈል ግዴታ ይሆናል፤ የመስመር ግዢ ዋጋ የሚጨምር ወይም የሚቀንስ ሆኖ ቢገኝ ወይም እንደ ወጣት ስብዕና መገንቢያ ማዕከሉ ተጨባጭ ሁኔታ ለማስተካከል እንደ አስፈላጊነቱ የዚህ የክፍያ መጠን በፕሮሰስ ካውንስሉ ሊሻሻልይችላል፤

5/ የዚህ መመሪያ አንቀፅ 19 ንዑስ-አንቀፅ 8 እስከ 9 የተደነገጉት ለመዝናኛ አገልግሎት ተጫርተው አገልግሎቱን በሚያቀርቡ አካላት ላይ ተፈፃሚነት አላቸው፤

6/ ማዕከላቱ የወጣቶች ፍላጎት ባገናዘበ መልኩ የሀገር እሴትና ባህልን የማይቃረን የተለያዩ ፊልሞች፣ ቲያትሮች እና ሌሎች የመዝናኛ ፕሮግራሞችን የወጣቶችን የመክፈል አቅም ባገናዘበ መሰረት በተደራጁ ወጣቶች መስጠት ይችላሉ፤

7/ የዚህ አንቀፅ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ለስራ ያልደረሱ እና ወላጆቻቸውን

2/ pool, foosball, play station, and DSTV services will be given to those youths who are organized and win the bidding;

3/ the amount of payment for indoor games will be decided by the process council of the centers by considering the financial status of the youths;

4/ when the service line is purchased on a contract basis like DSTV and play station, it is a must to pay birr five per person to only watch football, athletics, and other entertainment programs; if it is found necessary, the stated service charge may be amended by the process council if the price of the service line increases or decreases, or based on the tangible realities of the youth personality enrichment centers;

5/ the provisions stated under Sub-Article 8 to 9 of Article 19 of this directive shall be applicable to those parties who won the bidding and provide the service;

6/ the centers, based on the interest of the youths, and considering their financial status, may offer various films, theatres, and other entertainment programs which are not contrary to the country's values and culture using the organized youths;

7/ without prejudice to the provision of this Article, the center may facilitate free or

ያጡ ወይም ወላጆቻቸው ምንም ገቢ የሌላቸው ታዳጊ ህጻናት መሆናቸው ከተረጋገጠ በየፕሮግራሙ የነጻ ወይም የዝቅተኛ ክፍያ የሚሰጥበት እድል ማዕከሉ ሊያመቻች ይችላል፡፡

21. **<u>የቤት ዉጪ ጨዋታዎች አገልግሎት</u>**

ወጣቶች በማዕከላቱ የመረብ ኳስ፣ የቅርጫት ኳስ፣ የእጅ ኳስና ሌሎች ከቤት ውጪ የሚሰጡ የጨዋታ አገልግሎቶችን ያገኛሉ፡፡

22. <u>ሁለገብ የአዳራሽ አገልግሎት</u>

1/ ማዕከሉ የአዳራሽ አገልግሎት ለወጣቶች ወይም የወጣት አደረጃጀቶች፣ የአቻ ለአቻ ውይይት፣ ስብሰባ፣ ስልጠናዎችና በተቋሙ አስተዳደር ሲፈቀድ በነጻ የአዳራሽ አገልግሎት ያገኛሉ፤

2/ ለመንግስት ስራዎችና ስልጠና ከሆነ የጽዳት በቀን አምስት መቶ ብር የሚከፈል ይሆናል፤

3/ አዳራሹን ለመጠቀም የሚፈልጉ ግለሰቦች፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ለስብሰባ እና ስልጠና ከሆነ በቀን አንድ ሺህ ብር በመክፈል አዳራሹን ይጠቀማሉ፤

4/ ለሰርግ፣ ለወጣቶች የተዘጋጀ ባዛር እና ሌሎች ዝግጅቶች ሶስት ሺህ አምስት መቶ ብር በመክፈል አገልግሎቱን ማግኘት ይችላሉ፤

5/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ-አንቀፅ 2 እንደተጠበቀ ሆኖ ለወቅታዊ የመንግስት ስራዎች በልዩ ሁኔታ የማዕከሉ አስተደደር ያለክፍያ ሊፈቅድ ይችላል፤

6/ የክፍያ ሁኔታ በዚህ መመሪያ አባሪ በተደረገዉ የኪራይ መነሻ ዋጋ መሰረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

minimum payment for attending programs if the children are orphans and are not ready for work or their parents do not have any income.

21. **<u>Outdoor Games Service</u>**

The youth will get volleyball, basketball, handball, and other outdoor game services in the center.

22. **<u>Inclusive Hall Service</u>**

1/ the center will provide the hall service freely for peer discussions, meetings, and training of the youths or youth organizations upon the approval of same by the administration of the institution;

2/ five hundred birr shall be paid per day for cleaning purposes for public activities and training;

3/ if individuals and non-governmental organizations want to use the hall for meetings and training, they will pay one thousand birr per day;

4/ an individual shall pay three thousand five hundred birr and get services for weddings and bazaars and other events that are intended for the youth;

5/ without prejudice to Sub-Article 2 of this Article, the administration of the center, in special cases, may offer the hall freely for current issues of the government;

6/ the payment condition shall be applied based on the initial rental price which is attached to this directive.

## 23. የወጣቶች የሳይንስና የፈጠራ ሥራ አገልግሎት

1/ ማዕከሉ ወጣቶች ራሳቸውን በተለያዩ የሳይንስ እና የፈጠራ ተግባራት ላይ እንዲሳተፉ ለማድረግ የሚያግዝ መሆን አለበት፤

2/ ወጣቶች ስራዎቻቸዉን እንዲያሳድጉና ስራዎቻቸዉን የሚያሳዩበት አዉደ-ርዕይ የማመቻቸት፣ በተጨማሪም ሌሎች በጎ ፍቃደኛ ወጣቶችን በማሰበሳብ ለወጣቶች ስልጠና ማማቻቸት፣ የስልጠና ግብዓት ማመቻቸት እና ለስልጠና እና ለልምድ የሚሆኑ ክፍሎችን ማዕከሉ ያመቻቻል፤

3/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ-አንቀጽ 2 ላይ የተደነገገው ሃላፊነት በአይ.ሲ.ቲ. ባለሙያ በበላይነት ይከታተለዋል፡፡

## 24. በጎ ፈቃደኞችን የማስተባበር አገልግሎት

1. ወጣቶች የበጎ ፍቃድ አገልግሎቶችን እያከናወኑ ለሀገር፣ ለአካባቢያቸው፣ ለቤተሰቦቻቸው እና ለራሳቸው የሚጠቅሙ ተግባራትን እንዲያከናውኑ የወጣቶች ስብዕና መገንቢያ ማዕከላት ወጣቶችን በበጎ ፍቃድ አገልግሎት ያስተባብራሉ፤

2. ይኸውም ማዕከላቱ ወጣቶችን፡-

ሀ) በተለያዩ የስልጠና ተግባራት፤

ለ) ማዕከሉንና፤አካባቢያቸውን፤በማፅዳት፤

ሐ) በሰብዓዊ አገልግሎቶች (የደም ልገሳ፣ አልባሳትን ማሰባሰብ፣ የአረጋዊያን እና የአቅመ ደካሞችን ቤት እድሳት ማድረግ)፤

መ) ተማሪዎችን በማስጠናት፤

ሠ) መጽሃፍትን በማሰባሰብ፤

## 23. Scientific and Job Creation Services for the Youth

1/ the center should work towards helping the youth to engage in various scientific and innovative activities;

2/ the center will facilitate opportunities for the youth to develop their work, and prepare exhibitions to promote the thereof; as well as facilitate training for the youths by mobilizing other voluntary youths, training inputs, and rooms for training and experience sharing;

3/ An ICT expert shall supervise the specified responsibility stated under Sub-Article 2 of this Article.

## 24. Volunteers Coordination Service

1/ youth personality enrichment centers shall coordinate youths to engage in voluntary services that help them to carry out activities that benefit the nation, their environment, families, and themselves;

2/ the center shall help the youths to participate in:

A. various training activities;

B. cleaning the centers and their environment;

C. humanitarian services (blood donation, collecting clothes, renewing houses of the elderly and the weak);

D. helping students in their studies;

E. collecting books;

ረ) በወቅታዊ ሁኔታዎች በማሳተፍና አጋርነታቸዉን እንዲገልጹ በማድረግ በጎ ፍቃደኛ የህብረተሰብ ክፍሎችን በማሳተፍ የማስተባበር ሚና መወጣት ይጠበቅባቸዋል፡፡

F. engaging in current affairs and seek their solidarity, and playing a role in coordinating the participation of voluntary segments of the community;

25. ክበባትን የማደራጀትና የመደገፍ አገልግሎት

1/ በወጣት ማዕከሉ የወጣቶችን ስብዕና በማነጽ ረገድ አይነተኛ ሚና ያላቸውና ብዙሃኑን ወጣት የሚያሳትፉ ክበባት መቋቋም አለበት፤

2/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ-አንቀፅ 1 የሚቋቋሙት ክበባት የሚከተሉትን ማካተት አለባቸው፡-

ሀ) ስፖርትና መዝናኛ ክበብ፤

ለ) የአይ.ሲ.ቲ. ክበብ፤

ሐ) የሰላም ክበብ፤

መ) የተዋልዶ ጤና ክበብ፣

ሠ) የፈጠራና የሳይንስ ክበብ፤

ረ) የቤተ-መጽሀፍት ክበብ፤

ሰ) የበጎ ፈቃድ ክበብ፤

ሸ) የኪነ-ጥበብ ክበብ፤

ቀ) የጸረ-ሱስ ክበብ፤ የአካባቢ ጥበቃና እንክብካቤ ክበብ፤

በ) የሥርዓተ-ጾታ ክበብ፤

ተ) የምክክርና የሥነ-ልቦና ክበብ፤

ቸ) የሀገር ፍቅር ክበብ፤

ነ) የህገ-ወጥ የሰዎች ዝዉዉር መከላከከል ክበብ፤

ኘ) የሚኒ ሚዲያ ክበብ እና የመሳሰሉ ክበባት በማዕከላቱ መቋቋም አለባቸው፡፡

25. **Organizing and Supporting Clubs Service**

1/ clubs that will have paramount importance in building the personality of the youths and participate the majority of the youths must be established in the centers;

2/ the clubs to be established according to Sub-Article 1 of this Article should include the following:

A. sports and entertainment club;

B. ICT club;

C. peace club;

D. reproductive health club;

E. science and innovation club;

F. library club;

G. voluntary club;

H. art cub;

I. anti-drug use club; environmental protection club;

J. gender club;

K. counseling and psychology club;

L. patriotic club;

M. human trafficking prevention club; and

N. mini-media club

**26. <u>የገላ መታጠቢያ አገልግሎት</u>**

1/ በማዕከሉ ውስጥ የገላ መታጠቢያ አገልግሎት ለማግኘት በማዕከሉ የተቋቋሙ ክበባት አባላት ለቀዝቃዛ ሻወር ብር 2.00 (ሁለት ብር)፣ ለሙቅ ሻወር ብር 5.00 (አምስት ብር)፤ ለሌሎች ተጠቃሚዎች ቀዝቃዛ ሻወር ብር 5.00 (አምስት ብር) ለሙቅ ሻወር ብር 10.00 (አስር ብር) መከፈል ይኖርበታል፤

2/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) እንደተጠበቀ ሆኖ ለማዕከሉ ሠራተኞች በነፃ አገልግሎቱን ተጠቃሚ ይሆናሉ፤

3/ የክፍያ ሁኔታ በዚህ መመሪያ አባሪ በተደረገዉ የኪራይ መነሻ ዋጋ መሰረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

**27. <u>የኪነ-ጥበብና ሚኒ-ሚዲያ አገልግሎት</u>**

የወጣቶች ስብዕና መገንቢያ ማዕከላት ወጣቶች ቋንቋቸውን እና የስነ-ፅሁፍ ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ ሚኒ ሚዲያዎችን ማቋቋም አለባቸው፡፡

**28. <u>የአርት ስፖርት አገልግሎት</u>**

1/ በማዕከሉ የማርሻል አርት ስፖርት በዉሹ፣ ጅዶ፣ ቴኳንዶና ካራቴ አገልግሎት ይሰጣል፤

2/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ-አንቀፅ 1 የሚሰጠው ስልጠና አሰልጣኙ በሙያዉ የአሰልጣኝነት ስልጠና የወሰደ መሆኑን ከስፖርት ጽህፈት ቤት የዕዉቅና ሰርተፊኬት ያለዉ መሆን ይኖርበታል፤

3/ የክፍያ ሁኔታ በማዕከሉ ፕሮሰስ ካዉንስል የሚወሰን ሆኖ የወጣቱን የመክፈል አቅም ከግምት ዉስጥ ያስገባ መሆን ይኖርበታል፤

4/ የዚህ መመሪያ አንቀፅ 19 ንዑስ አንቀፅ (11) እስከ (12) የተደነገጉት ተጫርተው አገልግሎቱን በሚያቀርቡ አካላት ላይ ተፈፃሚነት አላቸው፡፡

**26. <u>Bathing Service</u>**

1/ the center will charge two birr for cold water shower service and five birr for hot water shower service for those members of the various clubs established in the centers; whereas, it will charge five birr for cold water shower service and ten birr for hot water shower service for other customers;

2/ without prejudice to Sub-Article 1 of this Article, employees of the center shall get the bathing service free of charge;

3/ the payment condition shall be applied based on the initial rental price that is attached to this directive.

**27. <u>Arts and Mini-Media Service</u>**

The youth personality enrichment centers should establish mini-media that will help the youth to develop their language skills and literature potential.

**28. <u>Art Sports Service</u>**

1/ the center shall offer martial art sports in wushu, judo, taekwondo, and karate;

2/ the trainer for the sports stated under Sub-Article 1 of this Article should have a certificate for a trainer and bring recognition for the thereof from the sports office;

3/ the payment condition shall be decided by the process council of the center based on the initial rental price that is attached to this directive; it will consider the financial status of the youths;

4/ the provisions stated under Sub-Article 11 and 12 of Article 19 of this directive shall be applicable to those parties who won the bidding and provide the service.

## 29. <u>የክብደት ማንሳትና የሰዉነት መገንባት አገልግሎት</u>

1/ የክብደት ማንሳትና የሰዉነት መገንባት አገልግሎት በወጣት ማዕከላት ዉስጥ ይሰጣል፤

2/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ-አንቀፅ 1 የሚሰጠው ስልጠና አሰልጣኙ በሙያዉ የአሰልጣኝነት ስልጠና የወሰደ መሆኑን ከስፖርት ጽህፈት ቤት የዕዉቅና ሰርተፊኬት ያለዉ መሆን ይኖርበታል፤

3/ የክፍያ ሁኔታ በማዕከሉ ፕሮሰስ ካዉንስል የሚወሰን ሆኖ የወጣቱን የመክፈል አቅም ከግምት ዉስጥ ያስገባ መሆንይኖርበታል፤

4/ የዚህ መመሪያ አንቀፅ 19 ንዑስ-አንቀፅ 8 እስከ 9 የተደነገጉት ተጫርተው አገልግሎቱን በሚያቀርቡ አካላት ላይ ተፈፃሚነት አላቸው፡፡

## 30. <u>የጂምናዚየም አገልግሎት</u>

1/ የጅምናዚየም አገልግሎት ያለ መሳሪያና በመሳሪያ የሚሰሩ የእንቅስቃሴ አይነቶች የሚያካትት ሆኖ በማዕከሉ የሚቀርብ ይሆናል፤

2/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ-አንቀፅ 1 የሚሰጠው ስልጠና አሰልጣኙ በሙያዉ የአሰልጣኝነት ስልጠና የወሰደ መሆኑን ከስፖርት ጽህፈት ቤት የዕዉቅና ሰርተፊኬት ያለዉ መሆን ይኖርበታል፤

3/ የክፍያ ሁኔታ በማዕከሉ ፕሮሰስ ካዉንስል የሚወሰን ሆኖ የወጣቱን የመክፈል አቅም ከግምት ዉስጥ ያስገባ መሆን ይኖርበታል፤

4/ የዚህ መመሪያ አንቀፅ 19 ንዑስ-አንቀፅ 8 እስከ 9 የተደነገጉት ተጫርተው አገልግሎቱን በሚያቀርቡ አካላት ላይ ተፈፃሚነት አላቸው፡፡

## 29. <u>Weight Lifting and Bodybuilding Service</u>

1/ weight lifting and bodybuilding services are provided at the youth centers;

2/ the trainer for the sports stated under Sub-Article 1 of this Article should have a certificate for a trainer and bring recognition for the thereof from the sports office;

3/ the payment condition shall be decided by the process council of the center based on the initial rental price that is attached to this directive, and it will consider the financial status of the youths;

4/ the provisions stated under Sub-Article 8 to 9 of Article 19 of this directive shall be applicable to those parties who won the bidding and provide the service.

## 30. <u>Gymnasium Service</u>

1/ the center shall provide gymnasium service that includes various activities that will be done with or without sports materials;

2/ the trainer for the sports stated under Sub-Article 1 of this Article should have a certificate for a trainer and bring recognition for the thereof from the sports office;

3/ the payment condition shall be decided by the process council of the center based on the initial rental price that is attached to this directive, and it will consider the financial status of the youths;

4/ the provisions stated under Sub-Article 8 to 9 of Article 19 of this directive shall be applicable to those parties who won the bidding and provide the service.

**31. የመረጃ አገልግሎት**

1/ በማዕከሉ የሚገኙ ወጣት ነክ መረጃዎችን በመያዝ ለወጣቶች ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎ ሊያደርጉ በሚችሉ ጥናቶች ላይ አስተዋጽኦ በማድረግ በማዕከሉ የወጣቶችን ተሳትፎ ለማሳየት መረጃዉ ተጠናቅሮ እንዲቀመጥ ያደርጋል፤

2/ የወጣቶችን ሁለንተናዊ መረጃ በጾታ፣ በዕድሜ፣ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት፣ ስራ ያላቸዉና የሌላቸዉ፣ በክበባት የተደራጁትን ወንድና ሴት እንዲሁም አጠቃላይ የማዕከሉን እንቅስቃሴ የሚያሳይ መረጃ ለይቶ በማስቀመጥ ለመረጃ ፈላጊዉ አካል የመረጃ ምንጭ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሶስት
## የተጠቃሚዎች መብት እና ግዴታ

**32. የተጠቃሚዎች መብቶች**

የማዕከላቱ ተጠቃሚ ወጣቶች የሚከተሉት መብቶች አላቸው፡-

1/ ማዕከሉ በሚያዘጋጃቸው የልማት ተግባራት መሳተፍ፤

2/ ማዕከሉ በሚያዘጋጃቸው ጉባኤዎች ላይ በመሳተፍ አስተያየት መስጠት፤

3/ በማዕከሉ ውስጥ በሚቋቋሙ ክበባት አባል በመሆን በትምህርት፣ በመዝናኛ፣ በድራማ፣ በሙዚቃና በመሳሰሉት መሳተፍ፤ እና

4/ የማዕከሉን አገልግሎት የማግኘት መብቶች አላቸው፡፡

**31. Information Service**

1/ youth-related information shall be kept at the center in a way to contribute for studies that help to ensure for an increased political, social, and economic participation of the youth and depicts the thereof;

2/ the center shall serve as a source of information for the concerned organs by maintaining the overall information of the youth by gender, age, economic status, employment and unemployment status, those who are organized in clubs as well as information that depicts the comprehensive activities of the center.

## Part Three
## Rights and Obligations of Beneficiaries

**32. Rights of the Beneficiaries**

Those youth beneficiaries of the centers shall have the following rights:

1/ participate in development activities prepared by the center;

2/ participate in assemblies organized by the center and express their ideas;

3/ be a member of the clubs established in the center and participate in educational, entertainment, dramatic, musical, and such other similar activities;

4/ getting other services provided by the center.

**33. የተጠቃሚዎች ግዴታ**

የማዕከላቱ ተጠቃሚ ወጣቶች የሚከተሉት ግዴታዎች አላቸው፡-

1/ ወርሃዊ የአባልነት መዋጮ መክፈል፤

2/ የአልኮልና የአደንዛዥ እጾችን ተጠቅሞ ወይም ይዞ ወደ ማዕከሉ አለመገባት፤ተጠቅሞ ወይም ይዞ የተገኘ ከአባልነት የሚሰረዝና በህግ የሚጠየቅ መሆኑን ማወቅ፤

3/ የማዕከላቱን ንብረት እንዳይባክንና እንዳይበላሽ መንከባከብ፤

4/ በማዕከሉ የሚወጡ ደንቦች፣ መመሪያዎችንና ውሳኔዎችን ማክበር፤

5/ በማዕከሉ ግቢ ወስጥ ጸብ ወይም አምባጓሮ አለመፍጠር፤

6/ የማዕከሉን ንብረት ሆን ብሎ የሰበረ መሆኑ በመረጃ ሲረጋገጥ ንብረቱን መተካት ወይም ገንዘቡን መክፍል፣

7/ ቁማርና ሌሎች አስነዋሪ ተግባራትን በማዕከሉ ውስጥ ፈጽሞ አለመገኘት፤

8/ የማዕከሉን ሰላም በሚያደፈርሱ ተግባራት ላይ አለመሰማራት፤

9/ ስለታም ነገሮችን እና የጦር መሳሪያዎችን ወደ ማዕከሉ ይዞ አለመግባት፤

10/ ስርቆትና የማጭበርበር ድርጊቶችን አለመፈጸም፣

11/ ሀይማኖት ነክ ስብሰባዎች እና ስርአቶችን በማዕከሉ ወስጥ አለማካሄድ፣

12/ ፖለቲካ ነክ ስብሰባዎች እና ስርአቶችን በማዕከሉ ወስጥ አለማካሄድ፤

**33. Obligations of the Beneficiaries**

Those youth beneficiaries of the centers shall meet the following obligations:

1/ pay membership fee;

2/ not using or having alcohols and drugs and entering into the center; understand that in doing so, he shall be canceled from membership and will be held liable;

3/ keep the properties of the center from wastage and damage;

4/ respect regulation, directives, and decisions issued by the center;

5/ avoid quarrels in the premises of the center;

6/ replace the property or pay in cash, when someone intentionally damages the property of the center and such is confirmed with evidence;

7/ avoid gambling and other immoral activities in the center;

8/ involving in activities that disrupt the peaceful atmosphere of the center;

9/ not bringing sharp objects and other weapons into the compound of the center;

10/ avoid theft and frauds;

11/ not conducting religious meetings and rituals in the center;

12/ not conducting political-related meetings and ceremonies in the center.

34. <u>በስነ-ስርአት ጉድለት ስለሚወሰዱ እርምጃዎች</u>

የማዕከሉ ደንብና መመሪያዎች ጥሰው የተገኙ ወጣቶች ላይ የሚከተሉትን እርምጃዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡-

1/ ተገልጋዮች አጥፍተው ከመቀጣታቸው በፊት ጉድለታቸውን እንዲያስተካክሉ ምክርና ተግሳጽ ይሰጣል፤

2/ በማዕከሉ በሚሰጠዉ ትምህርትና ምክር ተጠቅሞ ከጥፋቱ የማይታረም ወጣት የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፤ ሌሎች ወጣት ተጠቃሚዎች እንዲያዉቁት በማዕከሉ ሰሌዳ ላይ ይለጠፋል፤

3/ በማዕከሉ የስነ-ሥርዓት እርምጃ ዉሳኔ መሰረት ከጥፋቱ የማይመለስ ተገልጋይ ወጣት በማዕከላቱ እንዳይገለገል ይደረጋል፤

4/ ሌሎች ያልተጠቀሱ የዲስፕሊን ጉድለቶችን ጨምሮ በማዕከሉ ዉስጥ በሚቋቋም የዲስፕሊን ኮሚቴ የሚታዩ ይሆናል፤

5/ የዲስፕሊን ኮሚቴዉ ተጠሪነቱ ለማዕከሉ ስራ አስኪያጅ ሆኖ የሚከተሉት አባላትይ ኖሩታል፡-

ሀ) የማዕከሉ አገልግሎት ማስፋፋት ቡድን መሪ………………… ሰብሳቢ፤

ለ) አንድ የቤተ-መጻህፍት ባለሙያ …………………………. ጸሃፊ፤

ሐ) የማዕከሉ የስነ-ልቦና ባለሙያ ………………….……………… አባል፤

መ) ከክበባት ጥምረት ተወካይ 1 ወንድና 1 ሴት………………... አባል፤

ናቸው፡፡

6/ የኮሚቴው የስራ ድርሻ ለማዕከሉ ተገልጋዮች ብቻ ነው፤

7/ የዲሲፒሊን ኮሚቴው የውሳኔ ሃሳብ ለስራ

34. **<u>Measures to be taken due to Disciplinary Misconducts</u>**

The following measures shall be taken on those youths that contravene the rules and regulations of the center:

1/ advice and reprimands will be given to customers to correct their failures before they are punished;

2/ a written warning shall be given to a youth who fails to correct his wrongs using the lessons and advice given in the center; it will be posted on the notice board of the center to let other young users of the center know the case;

3/ a young customer who fails to rectify his offenses based on the given disciplinary measures of the center will be prohibited from using the center;

4/ other unspecified disciplinary problems shall be addressed by a disciplinary committee to be established in the center;

5/ the disciplinary committee shall, being accountable to the manager of the center, have the following members:

a) the center's service expansion team leader ---------- chairperson;

b) one librarian ------------ secretary;

c) psychologist of the center --------- --------------------------- member;

d) 1 male and 1 female representative from the clubs' coalition ---- member;

6/ the committee is only responsible for customers of the center;

7/ the discipline committee shall present a decision proposal to the manager;

አስኪያጁ ያቀርባል፤

8/ ስራ አስኪያጁም የውሳኔ ሃሳቡን የማጽናት ወይም የመሻር ወይም ቅጣቱን የማሻሻል ሙሉ ስልጣን ይኖረዋል፡፡ ሆኖም ከባድ የዲሲፒሊን እርምጃ ሲሆን ለፕሮሰስ ካውንስሉ ቀርቦ መጽደቅ ወይም መሻሻል አለበት፡፡

## ክፍል አራት

## የቦርድ አባላት ስብጥር፤ የፕሮሰስ ካዉንስል፣ የክፍለ-ከተማና የወረዳ የወጣቶችና ስፖርት ፅህፈት ቤት ተግባርና ኃላፊነት

35. የቦርዱ አባላት ስብጥር

1/ የወረዳ የወጣቶችና ስፖርት ጽህፈት ቤት ኃላፊ ……………… ሰብሳቢ፤

2/ የወጣት ፌደሬሽን ሰብሳቢ … ምክትል ሰብሳቢ፤

3/ የማዕከሉ ሥራ አስኪያጅ…………… ፀሐፊ፤

4/ የወረዳ የህብረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፍቃድ ማስተባበሪያ ፅህፈት ቤት ሃላፊ …………………. አባል፤

5/ የወረዳ የባህል፣ ኪነጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ሃላፊ………………. አባል፤

6/ የወጣቶች ስብዕና መገንቢያ ማዕከል ክበባት ጥምረት ተወካይ (2) …..… አባል፤

ይሆናሉ፡፡

36. ፕሮሰስ ካውንስል

1/ ፕሮሰስ ካውንስል በወጣቶች ስብዕና መገንቢያ ማዕከላት ውስጥ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

ሀ) የማዕከሉ ስራ አስኪያጅ ……… ሰብሳቢ፤

ለ) የማዕከሉ አገልግሎት ማስፋፋት ቡድን

8/ the manager shall have complete authority to approve or reject or rectify the given decision. However, if it is a grave disciplinary measure, it must be submitted to the process council for approval or amendment.

## Part Four

## Composition of the Board members; Duties and Responsibilities of the Process Council, and Youth and Sports Offices of the Sub-city and Woreda

**35. Composition of Board Members**

1/ head of the youth and sports office of the woreda ------------- chairperson;

2/ chairperson of the youth federation --------------------- deputy chairperson;

3/ manager of the center ------------------- secretary;

4/ head of the community participation and volunteerism coordination office of the woreda ------------------------ member;

5/ head of the culture, arts, and tourism office of the woreda ------- member;

6/ (2) representatives from the youth personality enrichment centers clubs coalition ------------------ member;

**36. Process Council**

1/ the process council shall have the following members in the youth personality enrichment centers:

A. manager of the center ---------------------------------------- chairperson;

B. the center's service expansion team leader -------- deputy chairperson;

መሪ………… ምክትል ሰብሳቢ፤

ሐ) የማዕከሉ ፕሮግራምና ስልጠና ኦፊሰር ………. ፀሐፊ፤

መ) የማዕከሉ የስነ-ልቦና እና ምክክር አገልግሎት ባለሙያ ……… አባል፤

ሠ) የማዕከሉ ፋይናስ ኦፊሰር………. አባል፤ ይሆናሉ፡፡

2/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ-አንቀፅ 1 የተዘረዘሩት የማዕከሉ ሰራተኞች በማይሟሉባቸው ሁኔታ የማዕከሉ ስራ አስኪያጅ እንደ አስፈላጊነቱ ከሌሎች የማዕከሉ ሰራተኞች መካካል የካውንስሉ አባል እንዲሆኑ ሊወክል ይችላል፡፡

## 37. <u>የማዕከሉ ፕሮሰስ ካውንስል ሃላፊነትና ተግባር</u>

1/ በሳምንት አንዴ የስብሰባ ጊዜ የማዕከሉን የስራ ክፍል የስራ እንቅስቃሴ ይገመግማል፤

2/ ማዕከሉ ለተደራጁ ወጣቶች የሚሰጡ የአገልግሎት አይነቶች የኪራይ ዋጋን ይወስናል፤

3/ የተደራጁ ወጣቶች በማዕከሉ የሚሰጡ አገልግሎቶችን ለወጣቶች የሚቀርቡበትን የዋጋ ተመን ይወስናል፤ መሻሻል ያለበት መሆኑ ከታመነበት ዋጋውን ያሻሽላል፤

4/ የማዕከሉን እቅድ በጋራ ያጸድቃል፤ ክንውኑን በተቀመጠው ቋሚ ጊዜ ሰሌዳ መሰረት ይገመግማል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

5/ ለሚያጋጥሙት ችግሮች የመፍትሄ አቅጣጫ ያስቀምጣል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

6/ የሌሎች አቻ ማዕከላትን የሥራ እንቅስቃሴ ተሞክሮ በመዉሰድ ተግባራዊ ያደርጋል፤

7/ ማዕከሉን ለማስፋፋትና ለማበልጸግ የሚያስችል እቅድ ነድፎ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፤

8/ የማዕከሉን አገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ለማሻሻል መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር በቅንጅት ይሰራል፡፡

C. the center's program and training officer --------------------- secretary;

D. the center's psychological and counseling service expert ---- member;

E. the center's finance officer ------------ --------------------------- member;

2/ where employees of the center that are stated under Sub-Article 1 of this Article are not present, the manager of the center shall delegate other employees of the center as may be found necessary.

## 37. <u>Responsibilities and Duties of the Process Council of the Center</u>

1/ evaluate the activities of the departments of the center in a meeting to be held once in a week;

2/ determine the rental price for the services to be provided for the organized youths by the center;

3/ determine the price of the services provided to the youth in the center by those organized youths; adjust the price if it is found necessary to do so;

4/ jointly approve the plan of the center; evaluate the performance of the thereof as per the specified schedule; follow up the implementation of same;

5/ set directions for solutions for the encountered problems; follow up the implementation of the thereof;

6/ share the experience of other equivalent centers and applies same;

7/ design plans that enable to expansion and enhance the center, and cause the implementation of the thereof;

8/ work in partnership with governmental and non-governmental organizations to improve the service delivery of the center.

## 38. የክፍለ-ከተማ የወጣቶችና ስፖርት ጽህፈት ቤት

1/ የወጣቶች ስብዕና መገንቢያ ማዕከላትን አጠቃላይ የስራ እንቅስቃሴ ይከታተላል፤ ይገመግማል፤ይደግፋል፤

2/ የወጣቶች ስብዕና መገንቢያ ማዕከላት ሀብትና ንብረት በአግባቡ ስራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

3/ በወጣቶች ስብዕና መገንቢያ ማዕከላት የሚሰጡ አገልግሎቶችን የማስፋፋትና ደረጃቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ ይደግፋል፤

4/ ለማዕከላቱ አስፈላጊ የሆኑ ግብአቶችን እንዲሟላ ያደርጋል፤

5/ በወጣቶች ስብዕና መገንቢያ ማዕከላት እድሳትና ጥገና እንዲከናወን ያደርጋል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

6/ የተሻለ አፈጻጸም ያላቸውን የወጣቶች ስብዕና መገንቢያ ማዕከላት ያበረታታል፤ እውቅና ይሰጣል፤

7/ የወጣቶች ስብዕና መገንቢያ ማዕከላት ያሉበትን ሁኔታ መረጃ ይይዛል፤ ተሞክሮዎችን ያስፋፋል፤

8/ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር በመቀናጀት የወጣቶች ስብዕና መገንቢያ ማዕከላት የሚጠናከሩበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

9/ በወረዳው የምልመላ ኮሚቴ ተመርጠው የቀረቡለትን እጩ ስራ አስኪያጆችን በመገምገም የውሳኔ ሀሳብ ለቢሮው ያቀርባል፤

## 38. Youth and Sports Office of the Sub-City

1/ follow up, evaluate, and supports the overall working activities of the youth personality enrichment centers;

2/ follow up and control the proper utilization of the resources and properties of the youth personality enrichment centers;

3/ follow up the expansion and standardization of the services provided by the youth personality enrichment centers; control and support the thereof;

4/ cause the provision of the necessary inputs for the centers;

5/ cause the execution of renovation and maintenance works for the youth personality enrichment centers; follow up the implementation of same;

6/ encourage best performing youth personality enrichment centers; give recognition for the thereof;

7/ maintain information on the status of the youth personality enrichment centers; expand best practices;

8/ facilitate conditions for strengthening the youth personality enrichment centers in collaboration with governmental and non-governmental institutions;

9/ evaluate the selected managers that were nominated and presented by the woreda recruitment committee; submit a decision proposal to the bureau;

10/የብቃት፣ የስነ-ምግባርና የአፈጻጸም ችግር ያለባቸውን ስራ አስኪያጆች በመገምገም ለስንብት የውሳኔ ሃሳብ ለቢሮዉ ያቀርባል፡፡

## 39. የወረዳ የወጣቶችና ስፖርት ጽህፈት ቤት

1/ የወጣቶች ስብዕና መገንቢያ ማዕከላትን አጠቃላይ የዕለት ተዕለት የስራ እንቅስቃሴ ይከታተላል፣ ይገመግማል፣ ይቆጣጠራል፣ ይደግፋል፣

2/ የወጣቶች ስብዕና መገንቢያ ማዕከሉ በስራ አፈጻጸም ሂደት ያጋጠሙትን ችግሮች እንዲፈቱ ያደርጋል፣

3/ የወጣቶች ስብዕና መገንቢያ ማዕከላት አቅም እስኪጎለብት የግብአት እና የበጀት ድጋፍ ያደርጋል፣

4/ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት፣ ከአካባቢው ህብረተሰብ እና ከታዋቂ ግለሰቦች ጋር በመቀናጀት የወጣቶች ስብዕና መገንቢያ ማዕከላት የሚጠናከሩበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣

5/ የወጣቶች ስብዕና መገንቢያ ማዕከላት ለታለመላቸው አላማ እንዲውሉ በኃላፊነት ይከታተላል፣ ችግሮች ሲያጋጥሙ ይፈታል፣

6/ የወጣቶች ስብዕና መገንቢያ ማዕከላት ዕጩ ስራ አስኪያጆች መልማይ ኮሚቴ ያቋቁማል፣ ምልመላው በስራ አስኪያጆች የሹመት መመሪያ መሰረት ስለመከናወኑ ያረጋግጣል፡፡

7/ በቢሮው የተሾመውን የማዕከሉን ስራ አስክያጅ የሹመት ደብዳቤ በማዕከሉ ቦርድ በኩል እንዲሰጥ ያደርጋል፡፡

10/ evaluate the exhibited competence, ethical, and performance problems of managers and present a decision proposal to the bureau for their dismissal.

## 39. Youth and Sports Office of the Woreda

1/ follow up, evaluate, control, and support the overall day-to-day activities of the youth personality enrichment centers;

2/ ensure that the problems of the youth personality enrichment centers that are encountered during the implementation process of activities are addressed;

3/ provide input and budget support for the youth personality enrichment centers until they develop their capacity;

4/ facilitate conditions for strengthening the youth personality enrichment centers in collaboration with governmental and non-governmental organizations, the local community, and prominent individuals;

5/ follow up responsibly that the youth personality enrichment centers are used for the intended purpose; address encountered problems;

6/ establish a section committee that nominate potential managers for the youth personality enrichment centers; ensure that the selection was undertaken according to the appointment directive for managers;

7/ give a letter of appointment to the manager of the center by the board of the center who is appointed by the bureau.

40. <u>ስለማዕከላቱ ወጪ አስተዳደር</u>

1/ ማዕከሉ ከሚሰበስበው ገቢ ለኮንትራት ሠራተኞች ክፍያ፣ ለሥራ ማስኬጃ እና ማዕከሉን ለማስፋፋት ሊያውለው ይችላል፡፡

2/ በአንድ ጊዜ ለሚደረግ ወጪ እስከ ብር 10,000.00 (አስር ሺህ ብር) በማዕከሉ ስራ አስኪያጅ አስቸኳይ ወጪ የሚጠይቁ ጉዳዮች ሲያጋጠሙ ወጪ ሊያደርግ ይችላል፤

3/ ከብር 10,001.00 /አስር ሺህ አንድ ብር/ እስከ ብር 50,000.00 (ሀምሳ ሺ ብር) በፕሮሰስ ካዉንስል ተወስኖ እና ጸድቆ ወጪ ሊደረግ ይችላል፤

4/ ከብር 50,001.00 (ሀምሳ ሺህ አንድ ብር) በላይ በቦርድ ተወስኖ እና ጸድቆ ለታለመለት ዓላማ የሚዉል ይሆናል፤

5/ በዚህ አንቀጽ የሚደረግ ክፍያና አጠቃቀም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርን የፋይናንስ ህግ እና መመሪያን የተከተለ መሆን አለበት፡፡

## ክፍል አምስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

41. <u>ስለ ማዕከሉ ስራ አስኪያጅ</u>

የማዕከሉ ስራ አስኪያጅ ቅጥር ብቃትና ችሎታን እንዲሁም ሹመትን መሰረት በማድረግ ይፈፀማል፡፡

42. <u>ሠራተኞች ቅጥርና አስተዳደር</u>

1/ የማዕከሉ ሰራተኞች ቅጥርና አስተዳደር በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግስት ሰራተኞች ህግ መሠረት የሚፈጸም ይሆናል፤

2/ የመንግስት ሰራተኞች ህግ ሳይቃረን ወጣቶች በማዕከሉ እንዲቀጠሩ ይደረጋል፤

**40. <u>Expense Administration of the Centers</u>**

1/ the center may utilize its revenues for payments of contract employees, operating costs, and the expansion of the center;

2/ the manager of the center may effect payments up to birr 10,000.00 (ten thousand birr) at a time in case of encountering urgent matters;

3/ expenses from birr 10,001.00 (ten thousand and one birr) to birr 50,000.00 (fifty thousand birr) may be determined ad approved by the process council and payments shall be made;

4/ expenses above birr 50,001.00 (fifty thousand and one birr) shall be determined and approved by the board, and payments will be made for the intended purpose;

5/ payments made and utilization of same as per this Article should be carried out according to the financial laws and directives of the Addis Ababa city government.

## Part Five
## Miscellaneous Provisions

**41. <u>About the Manager of the Center</u>**

The recruitment of the manager of the center shall be based on competence and capacity as well as appointment procedure.

**42. <u>Recruitment and Management of Employees</u>**

1/ the recruitment and administration of employees of the center shall be carried out based on the civil servants' law of the Addis Ababa city government;

2/ youths will be hired in the centers without contradicting the civil servants' law;

3/ የሰራተኞችን ጥቅማ ጥቅም የሲቪል ሰርቪስ መመሪያ በሚፈቅደዉ መሰረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

3/ benefits for employees shall be executed in accordance with the provisions specified under the civil servants' directive.

43. <u>ስለተጠያቂነት</u>

ማንኛውም ይህን መመሪያ ተላልፎ የተገኘ ሰው አግባብነት ባለው ህግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

**43. <u>Accountability</u>**

Any individual that contravenes this directive shall be held liable pursuant to the relevant laws.

44. <u>መመሪያዉን ስለማሻሻል</u>

ይህን መመሪያ እንደ አስፈላጊነቱ ቢሮው ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

**44. <u>Amending the Directive</u>**

The bureau may amend this directive as may be found necessary.

45. <u>መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ ከየካቲት 18 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**45. <u>Effective Date</u>**

This directive shall enter into force as of this 25th day of Feburary, 2022.

**አዲስ አበባ የካቲት 18 ቀን 2014 ዓ.ም**

**አብርሀም ታደሰ**

**አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ኃላፊ**

**Done at Addis Ababa, this 25th day of Feburary, 2022**

**Abraham Tadesse Kassaye**

**Head of the Youth and Sports Bureau of the Addis Ababa City Government**

# አባሪ 1፡ የማዕከላቱ የአገልግሎት አሰጣጥ ማጠቃለያ ሰንጠረዥ 1

| ተ.ቁ | የአገልግሎቱ አይነት | በነጻ የሚሰጡ አገልግሎቶች | በክፍያ የሚሰጡ አገልግሎቶች |
|---|---|---|---|
| 1 | የቤተ-መፅሀፍት አገልግሎት | የተለያዩ ትምህርታዊ መጽሃፍት፣ ልቦለዶች፣ ዲክሽነሪዎች፣ ኢንሳይክሎፒዲያዎች፣ ጋዜጦች፣ በራሪ ጽሁፎች፣ ወዘተ.... የተለያዩ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች፣ ትምህርታዊ ካሴቶች፣ ሲዲዎችና ዲቨዲዎች የተለያዩ ካርታዎች፣ ፍቶግራፎችና ታሪካዊ ምስሎች፣ የንባብና የዉሰት አገልግሎትና የዲጂታል ቤተ-መጽሀፍት አገልግሎት መስጠት | |
| 2 | የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ አገልግሎት | የተለያየ መረጃዎች ክፍት የስራ ቦታና የውጪ ትምህርት እድልና የተለያዩ የወጣቱን ስብዕና የሚገነቡ መረጃዎችን ማቅረብ | የኮምፒውተር ጽሑፍ፣ የመጠረዝ፣ ላሚኔት፣ የፎቶኮፒ፣ ኢንተርኔትና ኢሜል አገልግሎት |
| 3 | ወጣት ተኮር የጤና አገልግሎትና በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ ምክር እና ምርመራ አገልግሎት | የወጣቶች የጤና ፓኬጆች፣ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ምክርና ምርመራ አገልግሎት፣ የቤተሰብ ምጣኔ መረጃና የምክር አገልግሎት፣ የኮንዶም ስርጭት እንዲሁም የደም ልኬት ማድረግ | የስኳር መጠን መለካት፣ የደም አይነትን ማረጋገጥ የመሳሰሉት |
| 4 | የወጣት ተኮር የስልጠና አገልግሎት | ለወጣቶች የሚሰጡ ስልጠናዎች፣ በስራ እድል ፈጠራ፣ በአመራር ክህሎት፣ በሀብት አሰባሰብና ፕሮጅክት አቀራረጽ፣ በኤች.አይ.ቪ./ኤድስና በስነ-ተዋልዶ ጤና፣ በበጎ ፈቃድ አገልግሎት፣ በህይወት ክህሎት፣ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን መከላከል፣ የመጀመሪያ ህክምና | የኮምፒውተር፣ የተለያዩ የጥገና ስልጠናዎች<br><br>የኪነ-ጥበብ ስልጠናዎች፣ የቋንቋ ሰልጠናዎች፣ የሂሳብ አያያዝ ስልጠና እና ተያያዥ ስልጠናዎችና ሌሎችም በተመጣጣኝ ክፍያ ይሰጣል፡፡ |
| 5 | የስነ-ልቦና እና ምክክር አገልገሎት | የአቻ ለአቻ ውይይቶች፣ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረቱ የግልና የቡድን ምክክሮች፣ በሱስ ዉስጥ ለሚገኙ ወጣቶች የሚሰጡ የምክር አገልግሎቶች | |
| 6 | የሁለ-ገብ አዳራሽ አገልግሎት | ለወጣት አደረጃጀቶች፣ ለክበባት ለአቻ ለአቻ ውይይት፣ ለወጣቶች ኮንፈረንስና ሌሎችመድረኮች | ለግለሰቦች ወይም ለተቋማት ስብሰባ ለሰርግና ለሌሎች ዝግጅቶች |

| ተ.ቁ | የአገልግሎቱ አይነት | በነጻ የሚሰጡ አገልግሎቶች | በክፍያ የሚሰጡ አገልግሎቶች |
|---|---|---|---|
| 7 | የካፌና ሬስቶራንት አገልግሎት | | የለስላሳ መጠጦች፣ ሻይ፣ ቡና፣ ወተትና የምግብ አገልግሎት |
| 8 | የቤት ውስጥ ጨዋታ አገልግሎት | የቼዝ፣ የዶሚኖ፣ ዳማና ዳርት ጨዋታዎችና የመሳሰሉት | የጠረጴዛ ቴኒስ፣ ፕሌይስቴሽን፣ ፑል፣ ጆተኒ፣ ከረንቡላ፣ ዲ.ኤስ.ቲቪ. እና የመሳሰሉት ጨዋታዎች |
| 9 | የቤት ውጪ ጨዋታ አገልግሎት | የመረብ ኳስ፣ የቅርጫት ኳስ፣ የእጅና እግር ኳስ ጨዋታዎች | |
| 10 | የኪነ-ጥበብና ሚኒ-ሚዲያ አገልግሎት | ጠቃሚ መረጃዎችን በሚኒ-ሚዲያ የማስተዋወቅ | የኪነ-ጥበብ ስራዎች ማለትም ፊልም፣ የትያትርና ሌሎች የመዝናኛ ፕሮግራሞች |
| 11 | የሳይንስና እና የፈጠራ ስራ አገልግሎት | የተለያዩ የፈጠራ ተግባራትን ማከናወንና ማሳየት | |
| 12 | የአርት ስፖርቶች ስልጠና አገልግሎት | | ወርልድ እና ኢንተርናሽናል ቴኳንዶ፣ ጁዱ፣ ዉሹ፣ ኪክ ቦክስ፣ ካራቴና የመሳሰሉት |
| 13 | የወጣቶች የበጎ ፈቃድ አገልግሎት | ወጣቶች በበጎ ፈቃድ አገልግሎት እንዲያሳልፉ ማድረግ | |
| 14 | ክበባትን የማደራጀትና መደገፍ አገልግሎት | ክበባትን ማደራጀትና መደገፍ | |
| 15 | የገላ መታጠቢያ አገልግሎት | ለማዕከሉ ሰራተኞች | በክፍያ የሚሰጥ |
| 16 | የጂምናዚየም አገልግሎት | ------ | በክፍያ የሚሰጥ |
| 17 | የክብደት ማንሳትና የሰዉነት ግንባታ አገልግሎት | ------ | በክፍያ የሚሰጥ |
| 18 | የመረጃ አገልግሎት | የተለያዩ ወቅታዊ ወጣት ነክ መረጃዎችን መስጠት | |

**Table 1 - A summary of the Service Delivery of the Centers**

| No. | Types of Services | Services to be delivered freely | Services to be delivered with payment |
|---|---|---|---|
| 1 | Library service | Various textbooks, novels, dictionaries, encyclopedias, brochures, etc.<br>Various Proclamations, Regulations, and directives<br>Educational cassettes, CDs, and DVDs, various maps, photographs, historical images, reading and book loaning service, and digital library service | |
| 2 | Information Communication Technology | Providing various information on vacancies, scholarships, and information that shape the personality of the youth | Computer typing, binding, laminating, photocopy, internet, and email services |
| 3 | Youth-related health services and voluntary HIV/AIDS counseling and testing service | Youth-based health packages, voluntary HIV/AIDS counseling and testing service, family planning information and counseling service, condom distribution, as well as blood pressure measuring | Measuring blood glucose level, testing blood type, etc. |
| 4. | Youth-based training services | Training on job creation, leadership skill, resource mobilization, and project designing, HIV/AIDS and reproductive health, voluntary service, life skill, prevention of harmful traditional practices, provision of first aid | Computer skill, various maintenance training, art training, language training, accounting and other related training |
| 5 | Psychological and Counseling service | Peer discussions, individual and group counseling service (voluntary based), counseling services intended for those drug-addicted youths | |
| 6 | Inclusive Hall service | For youth organizations, clubs, peer discussions, youth conferences, and other events | Meetings for individuals and institutions, for weddings, and other programs |
| 7 | Café and Restaurant service | | Soft drinks, tea, coffee, milk, and catering service |
| 8 | Indoor games services | Chess, domino, *'Dama'*, dart, and similar others | Table tennis, play station, pool, foosball, billiard, DSTV, and |

| No. | Types of Services | Services to be delivered freely | Services to be delivered with payment |
|---|---|---|---|
| | | | other similar games |
| 9 | Outdoor Games service | Volleyball, basketball, handball, and football | |
| 10 | Artistic and mini-media service | Promoting useful information using mini-media | Artistic works like films, theatre, and other entertainment programs |
| 11 | Science and Innovation works | Carry out various innovation works and showcase the thereof | |
| 12 | Art sports training service | | World and international taekwondo, judo, wushu, kick-boxing, karate, and similar others |
| 13 | Youth voluntary service | Encourage the youth to involve in voluntary services | |
| 14 | Clubs organizing and supporting service | Organizing and supporting clubs | |
| 15 | Bathing service | For employees of the center | rendered through payment |
| 16 | Gymnasium service | | rendered through payment |
| 17 | Weight lifting and bodybuilding service | | rendered through payment |
| 18 | Information service | Providing various youth-related up-to-date information | |